# ባለፉት 24 ሰዓታት 1 ሺህ 560 የላብራቶሪ ምርመራ ተደርጎ 2 ሰዎች የኮሮና ቫይረስ ተገኘባቸው

May 3, 2020




ባለፉት 24 ሰዓታት ለ1 ሺህ 560 ሰዎች ምርመራ ተደርጎ 2 ሰዎች የኮሮና ቫይረስ እንደተገኘባቸው የጤና ሚኒስትሯ ዶክተር ሊያ ታደሰ አስታወቁ።

ሚኒስትሯ በፌስ ቡክ ገጻቸው እንዳስታወቁት ቫይረሱ የተገኘባቸው የ49 ዓመት ወንድ እና የ45 ዓመት ሴት ኢትዮጵያውያን ናቸው።

ከዚህ ውስጥ አንደኛው ከዝዋይ ወደ አዲስ አበባ መጥቶ የህክምና ክትትል በማድረግ ላይ ያለ ሲሆን፥ የውጪ ሃገር ጉዞም ሆነ በቫይረሱ ከተያዘ ሰው ጋር ንክኪ ሳይኖራቸው ናሙናቸውም ተኝተው ከሚታከሙ ህሙማን የተወሰደ ነው።

ሁለተኛዋ ቫይረሱ የተገኘባቸው ግለሰብ ደግሞ የስልጤ ወረዳ ነዋሪ ሲሆኑ በቤት ውስጥ ቅኝት እና አሰሳ የተለዩ ናቸው፡፡

አሁን ላይ በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ቁጥር 135 የደረሰ ሲሆን፥ 75 ሰዎች ከቫይረሱ አገግመዋል ነው የተባለው።

ከዚህ ውስጥ ስድስቱ ሰዎች አዲስ ያገገሙ መሆናቸውም ነው የተገለጸው።

አዲስ አበባ